በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
**THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**
**MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS**

*የፕሬስ መግለጫ* ***PRESS RELEASE***

## <u>አምባሳደሯ የሹመት ደብዳቤያቸውን አቀረቡ</u>

በስዊድን የኢፌዲሪ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው የተሾሙት አምባሳደር ወይንሸት ታደሰ ለስዊድኑ ንጉስ ካርል 16ኛ ጉስታፍ ፎልክ ኸበርተስ የሹመት ደብዳቤያቸውን አቀረቡ፡፡

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቃል አቀባይ ጽ/ቤት እንዳስታወቀው አምባሳደሯ ደብዳቤውን ባቀረቡበት ወቅት ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያና ስዊድን የቆየ ግንኙነት እንዳላቸው በመጥቀስ ኢትዮጵያ ባለፉት አስርት ዓመታት የሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ በለውጥ ጎዳና እንደምትገኝ አስረድተዋል፡፡ አገሪቱ ለኢንቨስትመንት ምቹ በመሆኗ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እየሆነች ከመምጣቷም በላይ በጎረቤት አገሮችና በአካባቢው ሠላም ለማስፈን እያደረገችው ያለውን አስተዋፅኦ ገልፀዋል፡፡

ንጉስ ካርል 16ኛ ጉስታፍ በበኩላቸው ሁለቱ አገሮች የቆየና ታሪካዊ የሆነ ግንኙነት እንዳላቸው፣ ኢትዮጵያ በጎረቤት አገሮች ሰላምን ለማስፈን እያደረገች ያለውን ጥረት አድንቀው ከዚህ በተጨማሪ በኤርትራ ያለው ሁኔታ እንደሚያሳስባቸው ገልፀዋል፡፡

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**
**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**
**ታህሳስ 26 ቀን 2006 ዓ.ም.**

P.O.BOX 393 TEL: 011 5 517345 FAX: 011 5 514300 E-mail: mfa.press@ethionet.et Website: www.mfa.gov.et